ክፍል3

# የአማራን ማንነት በአማራ ድርጅት

**በውጭ አገር የምንገኝ አማሮች የሥራ ድርሻችን ምንድነው?**

አሁን የእኛ ዋናው ተግባር መሆን የሚገባው የተለያዩ የድጋፍ(የእርዳታ) መንገዶችን መጠቀም ነው።እነኚህም መንገዶች፣

(1) ከአማራ ብቻ የተወለዱ ሳይሆን ግማሽ ጎናቸውም አማራ የሆነ፣እንዲሁም አማራው ለህልውናው የሚያደርገውን ትግል የተቀበሉ ኢትዮጵያዊያን "ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር" እንደሚባለው እንዲሰባሰቡ፣እንዲቀራረቡና አብረው እንዲመክሩ መደጋገፍ አሥፈላጊ ነው።

(2) ) በአገር ቤት የሚገኙ የአማራ ሥብስቦች፣ በህቡዕ አንድ አመራር የሚሰጥ የፖለቲካ ድርጅት እዚያው መሬቱ ላይ መፍጠር የግድ ነው ምክንያቱም ሥራው የሚሰራው አገር ቤት እሥከሆነ ድረስ በቅርብ ሆኖ ታግሎ የሚያታግልና ለውጤት የሚያበቃ ይሆናል ማለት ነው።
የፖለቲካ ድርጅት ውጭ አገር አቋቁሞ እሠራለሁ ማለት አማራውን ለማንቃትና ለገንዘብ አሰባሰብ ይጠቅም ይሆናል እንጅ፣የአገር ቤቱን ትግል በሪሞት ኮንትሮል መምራት አይችልም፣ውጤታማም አይሆንም።

(3)በውጭ አገር የሚገኙ የአማራ ድርጅቶችም ይሁኑ ሥብስቦች አንድ እንዲሆኑ መሥራት፣ አንድ ከሆኑም እርዳታችንም አመርቂ ሥለሚሆንና የትግሉም ጊዜ ሥለሚያጥር፣ወደአንድነቱ የመግፋት ድጋፍ አሥፈላጊ ነው።
(4) እንደእሥከዛሬው ጠላት እኛን መሥሎ በመካከላችን ገብቶ በአሉባልታም ሆነ በተለያዩ መንገዶች እንዳይበትነን፣ ተሰባስበን ያለፍንባቸውን ሁኔታዎች በዜናና ጥናት መልክ በመለዋወጥ ራሥን ማንቃት፣እርስ በእርስ በቀላሉ መናበብ መቻል፣
(5) ሎቢ ማድረግ፣ገንዘብ ማዋጣት እና በአጠቃላይ ወጣቱ ከእኛ የሚጠይቀውን ማሟላት ነው።

እኛ ውጭ አገር የምንኖር ወገኖች! በዕውነት ትግሉ ለድል እንዲበቃ በሙሉ ልብና ፍላጎት እንነሳ ካልን በቀን ከምናወጣው ወጭ በ2 እና 3 እጅ ቀንሰን በመኖር የወገኖቻችንን የሠቆቃ ጊዜ ማሳጠር እንችላለን።

እሥከዛሬ እንደታዘብኩት ግን የተጀመረው ትግል ወደፊት ገፍቶ ወያኔ እንዲወድቅ እንፈልጋለን፣እንመኛለንም።
እዚያው በቦታው ያሉት ወገኖቻችን ይዋደቃሉ፣ይደማሉ፣ይሞታሉ።
ያለ እኛ ድጋፍ፣እንርሱ ብቻቸውን ታግለው ነፃ እንዲያወጡን እንፈልጋለን።አንጋጠንም የምንጠብቀው ይህንኑ ነው።

የእኛ ድጋፍ የትግሉን ጊዜ እንደሚያሳጥረው የተረዳን አይመሥለኝም።
በትግል ላይ ላለው ወገናችን አጋር እንጅ ባላጋራ አለመሆናችንን በድጋፋችን ማሥመሥከር ይኖርብናል።

እኛ በምንችለው ሁሉ ማለትም በገንዘብም፣በዕውቀትም፣በጉልበትም ወዘተ ካልተረባረብን ሠቆቃውን እናራዝመዋለን፣ድልም አይገኝም።ከተባበርን እናሳጥረዋለን።እርዳታ አንድ ጊዜ ሠጥተን ድል እንጠብቃለን፣ይህ የማይታሰብ ነው።እርዳታ አንድ ጊዜ፣ሁለት ጊዜ፣ቢበዛ ሦሥት ጊዜ ያውም በሥንት ማጉረምረምና ማቅማማት እንሠጣለን። ከዚያ ቀጣይነቱን እጠራጠራለሁ።እንዲህ መሆን የለበትም። እርዳታችን እሥከድል መሆን ይገባዋል፣እንቃ እላለሁ።
ከመንግሥቱ ኃ/ማርያም ዘመን ጀምሮ ቁጥር ሥፍር የሌለው አማራ በብዛት ወደውጭ አገር ተሰዷል። ይህ ሁሉ አማራ ኢትዮጵያ ውሥጥ የሚታገለውን ወገናችንን ቢረዳ፣ድሉ በተወሰኑ ዓመታት በተጠናቀቀ ነበር።

እሥካሁንም ድረስ በብዛት"የራሷ አሮባት የሰው ታማሥላለች" እንዲሉ የኢትዮጵያ አንድነት በልምምጥ ይመጣ ይመሥል፣ ሌሎችን እሥከመገንጠል የሚያቀነቅኑትን ጭምር እየተለማመጠና እያነበደደ፣በአማራ አንድነት መቆም አቅቶት የብዙ ጥቂት ሆኖ ዘሩን እያሥጨረሰ የሚገኘውም አማራው ነው።

ጠላቶቻችን ከውጭ አገር ጀምሮ በአገርም ውስጥ ያለውን፣ ከአማራውም፣ከኦሮሞውም ከሌሎቹም ጎሳዎች፣ ሆዳሞቹን ይዘው እያባበሉና በገንዘብ እየደለሉ በወገናችን ላይ ሲያዘምቱበት ልባችን ይደማል።የብዙ ጥቂት መሆናችን

ሳያንሰን፣እንርዳ ብለን የተነሳነውም የውዴታ ግዴታችንን በአግባቡ እየተወጣን ነው ወይ ብለን በቅንነት ራሳችንን እንጠይቅ። ወገኖቻችን በደም የሚከፍሉትን እንዴት እኛ በገንዘብና በአንዳንድ ሥራዎች መድማት ይሳነን። ድል ያለመረዳዳትና ያለመደጋገፍ አይመጣም።

ወገናችንን በሙሉ ልብ ደግፈን በቁርጠኝነት እንነሳ፣እጃችንንም እንዘርጋ፣አንሡሥት።ይህ የሚያልፍ ቀን እንዳያሥተዛዝበን፣ወገናችንን እንደግፍ፣ለድልም እናብቃው።ዛሬ ነው ወገን ለወገኑ መቆም ያለበት፣ነገ አይደለም።ልብ ያለን ልብ እንበል።

<u>ማሳሰቢያ</u>! እንርዳ ብለን ከመነሳታችን በፊት የእያንዳንዱን ድርጅት ምንነት ጠንቅቆ ማወቅ አሥፈላጊ ነው። አለበለዚያ በሥሜት ብቻ ተመርተን የምናደርገው እርዳታ ወደማይፈለገው ካዝና የገባ እንደሆን መናደድና እርም ማለትን ያሥከትላል።ይህም ሲባል እጅ እንሰብሰብ ማለት አይደለም። ወሬና ዜና እንለዋወጥ እጅ ለመዘርጋት።በራሳችን ንዝህላንነትና ሥህተት እርም ማለት ደረጃ መድረስ ለቀጣዩ ትግላችን እንቅፋት ነውና እናጣራ፣እንርዳ!

**<u>ኢትዮጵያ ውስጥ የአማራ ድርጅት መኖር ጥቅሙ ከብዙ በጥቂቱ</u>**

(1ኛ) ለትግሉ ጥንካሬ በቅድሚያ የአማራ ዘር የተባለ ከጎንደርና ከጎጃም ባሻገር፣ከደቡብ ኢትዮጵያ ጀምሮ የወሎንና የሸዋን አማራ ጨምሮ በአማራ አንድነት ተሰባስቦ በአንድ አመራር እንዲታገል ያሥተባብራል።
ይህ የሚጠቅመው ባለፈው እንደተደረገው ሁሉም ነገዶች የጎሳዎቻቸውን ተወካዮች ለሽግግር መንግሥት ሲያዘጋጁ፣አማራው ያለተወካይ ቀርቶ እንደተጠቃው "ሞኝን እባብ ሁለት ጊዜ ነደፈው" እንዳይሆን ይረዳዋል።

(2ኛ)አማራው ዛሬ ራሱ በህይወቱ እየከፈለ የሚያገኛቸውንና የሚያሥመዘግባቸውን ድሎች በራሱ ለአማራው ፍላጎት በተቋቋመው በአማራው ድርጅት እንዲጠበቅለት ያሻል። የአማራ ድርጅት ከሌለው ግን እንደከዚህ ቀደሙ ባለቤት የሌለው ቤት ይሆንና በኢትዮጵያ አንድነት ሽፋን በሚያደቡ የሥልጣን ጥመኞች የመቀማትና የመኮላሸት ዕጣ ፈንታ ይገጥመዋል ማለት ነው።
አማራው ድሎችንና በጎ ነገሮችን እያሥመዘገበ፣በጓዳ በር ብቅ ለሚሉ በላተኞች አሣልፎ ሲሰጥ እንደኖረው ሳይሆን የሚያሥመዘግባቸውን ድሎች ለእራሱ ለአማራው መጠናከሪያ መሆን ይኖርባቸዋል።ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል እንዳይሆን ያሻል።

(3ኛ) ከሌሎች ጎሳዎችም ጋር አብሮ ለመዎያየትም ፣ለመቀራረብም ሆነ አብሮ ለመሥራት፣ ብሎም ወያኔ ከገባበት ወቅት አንስቶ የጠፋውን፣ነገር ግን በአፍ የምንደጋግመውን የኢትዮጵያ አንድነትም ለማምጣት፣ ከእንግዲህ በሚወክለው የአማራ ድርጅት አማካይነት እንጅ በሞግዚት አይሆንም ማለት ነው።

<u>ማጠቃለያ</u>!
(1) ዛሬ ትግሬዎች በአማራው ዘር ላይ በአዋጅ የተደገፈ ዘግናኝ የዘር ማጥፋት ዘመቻ በሚያካሂዱበት ወቅት፣አማራው በመኖርና ባለመኖር መካከል የሚገኝ ሕዝብ ሆኗል።ይህ በመንግሥት ተብዬው ጦርነት የታወጀበት ሕዝብ!

**እንኳን ለኢትዮጵያ አንድነትና ለአገር ሉዐላዊነት ሊቆም ቀርቶ፣ ለራሱም ህልውና መቆም አዳግቶታል።ከእንግዲህ ወዲህ ከሁሉ በፊት ቅድሚያ ሠጥቶ መታገል ያለበት ራሱን ከመጥፋት ለማዳንና ህልውናውን ለማረጋገጥ የራሴ በሚለው በአማራ ድርጅት መሪነት በአማራነትና ለአማራ ማንነት መሆን ይገባዋል።**

**የአማራው ድርጅት አማራን ከዳር እሥከዳር አሥታጥቆ፣ዘረኛውን የትግሬ ወራሪ ኃይል አሽቀንጥሮ መጣል ከተግባሮቹ ዋነኛውን ቦታ ይይዛል።**

**ይህንን ቅድሚያ ሠጥቶ ሳይሰራ ወደሌላ እረማመዳለሁ ብሎ ካሰበ እንደገና መጥፊያውን አመቻቸ ማለት ነው።ቀጥሎም መብቱንና ማንነቱን ከማሥከበርም ባሻገር ከሌሎች ጎሳዎች ጋር የጀመረውን ሕዝባዊ ትብብር ወደፊት እንዲገፋበት ያሻል።ብሎም እሥከ ኢትዮጵያ አንድነት ለመዝለቅ ይጥራል።**

(2) አማራው የአማራ ማንነቱን ለማሥከበር ሲደራጅ ፣ቁጥራቸው የማይናቅ ወገኖች"ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነቱ ነው የሚያዋጣው" ይላሉ።ይህ አባባል ሙሉ በሙሉ ሥህተት ነው።

ምክንያቱም ሸዌ ከሸዋ ፣ጎንደሬ ከጎንደር፣ወሎዬ ከወሎ፣ጎጃሜ ከጎጃም፣ወዘተ ክፍላተ ሀገራት የተፈጠሩናየመነጩ አማሮች መጠሪያ ሲሆን፣
የእነዚህ ሁሉ የወል ሥም፣አማራና አማራነት ነው።ወያኔ በተናጠል በሸዌነት በጎንደሬነት በወሎዬነትና በጎጃሜነት ከሚታገለን በወል መጠሪያችን በአማራነት ተሰባስበን ብንገጨው ጠቀሜታው ለእኛው ነው።
አማራነት ከእየጎጦቻችን ማለትም ከሸዌነት፣ከጎንደሬነት፣ከጎጃሜነት ከወሎዬነት ወዘተ በላይ መሆኑን ከተረዳን ኢትዮጵያዊነትም ከአማራነት በላይ መሆኑን መቀበል አያዳግትም።ይህ ለሁሉም ግልፅ ይመሥለናል።

ይህንን መከራከሪያ የሚያቀርቡትን ወገኖች በሁለት መንገድ እከፍላቸዋለሁ፣
አንደኛው ወገን ቅንነትና የዋህነት ያልተለየው ግን ፍላጎቱና ምኞቱ አሸንፎት፣የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ለማገናዘብ አቅም ሥላነሰው፣በአማራነትና በኢትዮጵያዊነት መካከል ያለውንም ልዩነትና አንድነት በቅጡ ለመረዳት አላሥቻለውም።

ሌላኛው ወገን ደግሞ የፈጠረውን የኢትዮጵያ አንድነት ተብየው ድርጅት ለማንቀሳቀስ በአሁኑ ጊዜ ከአማራው ውጭ በአባልነትና በአጃቢነት ብዙም ደጋፊ ሥለማያገኝ፣አማራውን በአማራ ማንነት እንዳይቆም "አማራ ካልክ ኢትዮጵያዊነትህን ክደሀል" በማለት በማሥፈራሪያነት ይጠቀማል።

ማሥፈራሪያው ከዕውነት የራቀና ማደነጋገሪያ ነው። ኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት አለች፣ከግራኝም ሆነ ከኦሮሞ ወረራዎች በፊትም በኋላም አለች፣ኤርትራም ሳትገነጠል ኢትዮጵያ አለች፣ኤርትራም ተገንጥላ ኢትዮጵያ አለች።ኢትዮጵያ ሥትሰፋም ሥትጠብም እዚህ ደርሳለች። ዕውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ "ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ" የሆነ ክርክር ምንም ፋይዳ አይኖረውም።
ያው እንደለመዱት አማራ እንዳይደራጅና እንዳይመክት፣በተናጠል እንዲመታና እንዲጠፋ ካልሆነ በሥተቀር።

ከሽግግር መንግሥት ተብየው ጀምሮ ሁሉም ጎሳዎች በዘራቸው ተደራጅተውና ተሰባስበው የጎሳዎች መንግሥት አቋቁመው ሲገፉበት፣አማራው "የኢትዮጵያን አንድነት ብቻውን ያመጣ ይመሥል" 25ዓመት ተጉዞበት የአማራ ማንነቱን ያጣበት እንዲሁም ሲገደልበት፣ ሲመታበት፣ መሬቱንና ሚስቱን ከልጆቹ ጭምር ሲያሥረክብበት የኖረ መንገድ ሥለሆነ ለሦሥተኛ ጊዜ ወደውድቀት እንዳንወስደው እንጠንቀቅ።

ይህን ያጣውን የአማራ ማንነቱን ለማሥመለስ ደፋ ቀና በሚልበት በአሁኑ ወቅት በሙሉ ልብ እንዳይታገል በአማራነትና በኢትዮጵያ አንድነት መካከል ለማዋለል፣ለማማለልና እንደገና እንዲመታ መጣር እንዳይሆን፣የኢትዮጵያ አንድነት የምትሉ አማሮች አማራው በአማራነት መደራጀቱን አትቃወሙ፣ እንደገና ራሳችሁን መርምሩ።
እናንተም ለዚህ እንዲጠፋ ለተፈረደበት ዘር ኃላፊነት አለባችሁ።

ቀኝም ነፈሰ ግራ አማራው! ትግሉን አሁን እደረሰበት ደረጃ አድርሶታል። ትግሉ ይቀጥላል።መውደቅ መነሳት ያለ ነው።ይህንንም ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት የግድ ይላል።

ምንም እንኳን የአማራ ሕዝብ ከራሱ አብራክ በወጡትም ጭምር ብዙ ግፍ ቢሠራበትም፣በራሱ በአማራ ሕዝብ፣ድርጅትና ኃይል የአማራን የመኖር ዋስትና ማንነትና ህልውና ተግባራዊ ያደርጋል!

ሞት ለወያኔ ትግሬዎችና ግብረአበሮቻቸው

አያሌው ፈንቴ